በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የመ/ቁ/212950
ህዳር 30/2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡ ሰለሞን አረዳ**

**እትመት አሰፋ**

**ኑረዲን ከድር**

**መላኩ ካሳዬ**

**እስቲበል አንዱዓለም**

**አመልካች፡ አቶ ቶቼኖ ቶማ**

**ተጠሪ፡ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ**

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጧል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የውንብድና ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ የወንጀል ህግ አንቀፅ 670 ድንጋጌን ጠቅሶ በወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት አመልካች የተጠቀሰውን የወንጀል ህግ ድንጋጌን በመተላለፍ የማይገባውን ብልፅግና ለራሱ አልያም ለሌላ ሰው ለማስገኘት አስቦ በክሱ ዝርዝር ውስጥ በተገለፀው ቀን፣ ቦታ እና ሰዓት የግል ተበዳይ ወደሆኑት ወ/ሮ አበበች ባደቦ የንግድ ቤት በመሄድ የተበዳይን ጉረሮ አንቆ በመያዝ አንገታቸው ላይ የነበረ የዋጋ ግምቱ ብር 50,000(ሃምሳ ሽህ) የሚያወጣ 20 ግራም የወርቅ ሀብል፤ እንዲሁም ባንኮኒ ውስጥ የነበረውን ብር 20,000(ሃያ ሺህ) ወስዶ በኃሮ በኩል ያመለጠ በመሆኑ የውንብድና ወንጀል ፈፅሟል የሚል ነው፡፡

አመልካች ለዚሁ ክስ በሰጠው መልስ ድርጊቱን እና ጥፋተኝነቱን ክዶ በመከራከሩ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው እንዲሰሙ ከተደረገ በኋላ እንደክሱ አቀራረብ አስረድተዋል በሚል አመልካች ክሱን እንዲከላከል ታዟል፡፡ አመካችም አራት መከላከያ ምስክሮችን አሰምቷል፡፡ የመከላከያ ምስክሮቹም አመልካች እና የግል ተበዳይ ባል እና ሚስት የነበሩ መሆኑን፤ ክስ የቀረበበት ድርጊት ተፈፀመ ከተባለ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኋላ በዚያው ጉዳይ ሁለቱን ለማሸማገል ሽምግልና ተቀምጠው የነበረ መሆኑን፤ በዚሁ ጊዜ የግል ተበዳይን ስለድርጊቱ ሲጠይቋቸው አመልካች ንብረት ዘርፎኛል በሚል የከሰሷቸው ዘወትር ሰክሮ እየሄደ ስለሚረብሻቸው እንጂ የተወሰደባቸው ንብረት እንደሌላ የነገሯቸው መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤትም ለጉዳዩ አወሳሳን ይረዳኛል በማለት የሽማግሌዎቹ ሰብሳቢ የነበሩትን ፓስተር ታደሰ ታንቱ የተባሉትን ግለሰብ አስቀርቦ ሰምቷል፡፡ ተጨማሪ ምስክሩም አመልካች እና የግል ተበዳይ ባልና ሚስት መሆኑቻውን፤ ክስ የቀረበበት ጉዳይ ተፈፀመ ከተባለ በኋላ የሁለቱን ጉዳይ በሽምግልና የተመለከቱ መሆኑን፤ በሽምግልናው ላይም የግል ተበዳይ በእርግጥም ዝርፊያ ተፈፅሞባቸው እንደሆን በሚል የጠየቋቸው መሆኑን፤ ተበዳይም አመልካች ዘወትር ሰክሮ ንግድ ቦታቸው እየሄደ ስለሚረብሻቸው ለመከላከል በሚል የከሰሷቸው እንጂ የተፈፀመባቸው ውንብድና እንደሌለ የነገሯቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙ ክርክር መርምሮ እና የቀረቡትን ማስረጃዎች መዝኖ የዐቃቤ ህግ ክስ እና ማስረጃ ተስተባብሏል በሚል አመልካችን ከቀረበባቸው ክስ በነፃ አሰናብቷል፡፡ ይህንኑ ውሳኔ በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በመከላከያ ማስረጃው ያስመሰከረውን ፍሬ ነገር አስምልክቶ በዋናው ክርክር ወቅት በመስቀልኛ ጥያቄ ያስተባበለው ነገር የለም፤ ከተበዳይ ጋር ተደርጓል የተባለውን የእርቅ ስምምነት አስምልክቶም በጽሑፍ የቀረበ የእርቅ ስምምነት የለም፤ የድርጊቱ አፈፃፀምም አመልካች ከግል ተበዳይ ጋር የነበረው ጋብቻ ከተቋረጠ በኋላ ጉልበቱን በመጠቀም ለማስቀጠል ፍላጎት ያለው መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ድርጊቱ ከውንብድና ወንጀል ይልቅ በማስገደድ መጠቀም ወንጀልን የሚያቋቁም ነው በማለት ክስ የቀረበበትን አንቀፅ ወደ አንቀፅ 713 በመቀየር አመልካችን ጥፋተኛ ብሎት በ1 ዓመት ከ2 ወር ቀላል እስራት እና በብር 2,000(ሁለት ሺህ) የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ነሓሴ 14/2013 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያለውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሶ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም አመልካች የዐቃቤ ህግ ክስ እና ማስረጃን አላስተባበለም በሚል በወንጀል ህግ አንቀፅ 713 ስር ጥፋተኛ ተብሎ የመቀጣቱን አግባብነት በወንጀል ጉዳት ተከሳሽ የሆነ ሰው በመከላከያ ማስረጃው ማስረዳት ከሚጠበቅበት የማስረዳት ደረጃ አኳያ መርምሯል፡፡

በወንጀል ጉዳይ ዐቃቤ ህግ ያቀረበውን ክስ አስረድቷል የሚባለው ባቀረባቸው ማስረጃዎች ክሱን በቂ እና አሳማኝ በሆነ መልኩ ሲያስረዳ እንደሆነ የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 141 ይደነግጋል፡፡ በወንጀል ክሱ ተከሳሽ የሆነው ሰውም የቀረበበትን ክስ አስምልክቶ ማስተባበያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚታዘዘው ይኸው ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ከወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 141 እና 142 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ አንድ ሊነሳ እና መልስ ሊሰጠው የሚገባው ነጥብ "በወንጀል የተከሰሰ ሰው በመከላከያ ማስረጃው ማስረዳት/ማረጋገጥ/ የሚጠበቅበት የማስረዳት ደረጃ ምን ያክል ነው?" የሚለው ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ በወንጀል ተከስሶ ክሱን እንድከላከል ከተነገረው ተከሳሽ የሚጠበቀው ዐቃቤ ህግ ባስረዳው ልክ በመከላከያ ማስረጃው በቂ እና አሳማኝ በሆነ መልሉ መረጋገጥ ነው ወይስ የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ላይ ጥርጣሬ እንዲፈጠር ማድረግ ነው እንደማለት ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እንግዲህ ከላይ እንደተመለከተው በወንጀል የተከሰሰ ሰው መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚታዘዘው በዐቃቤ ህግ ማስረጃ የተረጋገጠበትን ክስ እና ማስረጃን እንዲያስተባብል ነው፡፡ ማስተባበል ማለት ደግሞ የተከሳሹን የወንጀል ድርጊት እና ጥፋተኝነት አረጋግጠዋል በተባሉት ማስረጃዎች ላይ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ጥርጣሬ እንዲፈጠር በማድረግ በማስረጃዎቹ የማስረዳት አቅም ላይ መተማመን እንዳይኖር ማድረግ ስለመሆኑ ከማስረጃ ህግ መሰረተ ሀሳብ እና በዚሁ ዙሪያ ከተደረጉ የምርምር ፅሁፎች የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከተከሰሰው ሰው የሚጠበቀው በመከላከያ ማስረጃው በቂ እና አሳማኝ በሆነ መልኩ ማስረዳት ሳይሆን የዐቃቤ ህግ ማስረጃን አስመልክቶ ቀድሞ በተያዘው አቋም ላይ ጥርጣሬን መፍጠር ብቻ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ዐቃቤ ህግ ክሱን ለማረጋገጥ ያቀረበው የሰው ምስክር ብቻ ነው፡፡ ቀርበው የተሰሙት የዐቃቤ ህግ ምስክሮችም እንደ ክሱ አቀራረብ አመልካች በግል ተበዳይ ላይ የውንብድና ወንጀል ሲፈጽም መመልከታቸውን ተናገረዋል፡፡ ሆኖም አመልካች ከተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዘ በአመልክች እን የግል ተበዳይ መካከል ሽምግልና ተቀምጠው የነበሩት የአመልካች መከላከያ ምስክሮች እና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማጣሪያ ምስክርነት የተሰሙት ሽማግሌዎቹ ሰብሳቢ የግል ተበዳይዋ በሽምግልናው ላይ አመልካችን በወንጀል የከሰሷችው ዘወትር ሰክሮ በመሄድ ስለሚረብሻቸው እንጂ የፈፀመባቸው የወንብድና ድርጊት እንደሌለ የነገሯቸው ስለመሆኑ ተናግረዋል፡፡ በእንዚህ አሸማጋይ ሽማግሌዎች ይህ ሁኔታ መረጋገጡ ቀድሞ በተሰሙት የዐቃቤ ህግ ምስክሮች የምስክርነት ቃል ላይ ጥርጣሬ እንዲኖር የሚያደርግ ነው፡፡

ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአመልካች እና የግል ተበዳይ መካከል ተደርጓል የተባለው የእርቅ ስምምነት በፅሁፍ አልቀረበም፣ እንዲሁም አመልካች በመከላከያ ማስረጃው ያረጋገጠውን ፍሬ ነገር በመስቀልኛ ጥያቄ አልጠየቀም በሚል ምክንያት የአመልካችን መከላከያ ማስረጃ ውድቅ ማድረጉ የቀረበው ጉዳዩ የወንጀል ክርክር መሆኑን እና በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ የሚጠበቅበትን የማስረዳት ደረጃ ያላገናዘበ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/34748 ላይ ግንቦት 04/2013 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔን በማፅናት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/36060 ላይ ነሐሴ 04/2013 የሰጠው ትዕዛዝ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁር 195(2(ለ(2))) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/46898 ላይ ታህሳስ 19/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካችን ከተከሰሰበት ወንጀል ነፃ በመልቀቅ የሰጠው ውሳኔ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(2(ለ(2))) ፀንቷል፡፡

## <u>ትዕዛዝ</u>

1. አመልካች በዚህ መዝገብ ላይ ከተከሰሰበት ወንጀል በነፃ የተሰናበተ በመሆኑ በሌላ ወንጀል የማይፈለግ መሆኑን አረጋግጦ በአስቸኳይ ከእስር እንዲለቀው ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡

2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም